የሰፊው ሕዝብ ድምፅ
ለሰፊው - ሕዝብ
(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣!)
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ
መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)
All ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME'ISONE)

39ኛ ዓመት ቁጥር 1 ጥቅመት 2006

# ትግላችን - ከእንግዲህ ወዴት? እንዴት?

በአለፉት ጥቂት ወራት በሃገር ውስጥ በህጋዊነት ታውቀው የሚንቀሳቀሱ ዴሞክራትና አገር ወዳድ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዲሁም ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ከግንቦት 97 ወዲህ ባልታየ ሁኔታ ከወያኔ የሚጠበቀውን አፈናና ወከባ እየተቋቋሙ በሰላማ ዊ ሰልፎችና ሌሎች የሰላማዊ ትግል ስልቶች ህዝባችንን እያንቀሳቀሱና የሚጠበቀውን መስዋእትነት እየከፈሉ ይገኛሉ። እንዲህ አይነቱ እንቅስቃሴ በማንኛውም ዴሞክራትና አገር ወዳድ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ መደገፍና መበረታታት ያለበት ነው። ሃገራችን በወያኔ/ኢህአዴግ ፀረ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ከወደቀችበት ጊዜ አንስቶ ህዝባችን በተለይ ግንቦት 97 ላይ ከነዚህ ዛሬ ከምንታዘባቸ ው ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች እጅግ በሰፋ ሁኔታ በሚልዮን እየተቆጠረ ከዳር አስከዳር ተንቀሳቅሶ ከባድ መስዋእትነትም የከፈለባቸ ውም ቢሆኑም የታለመውን ፍሬ ያላስገኙ ትግሎች አካሂዷል። በመሆኑም ይህ አሁን የተቀሰቀሰው ህዝባዊ ትግል ከአሁኑ ሰፍቶ ሚልዮኖችን ያካተተ ህዝባዊ የትግል ማእበል እንዲሆን ብቻ ሳይሆን ቀጣይነቱ ተረጋግጦ ለድል እንዲበቃ ምን ማድረግ ያስፈልጋ ል? ምን ማድረግ ይቻላል የሚሉትን ጥያቄዎች በጥሞና አንስቶ መመለስ የዜግነት ግዴታው ነው። ለዚህ ከባድና ውስብስብ ጥያቄ መኢሶን "መፍትሄው ይኸ ነው"ብሎ የሚሰነዝረው አንድ ወጥና ቀላል ሃሳብ የለውም። ከዚህ ይልቅ ዛሬ ከምንገኝበት ዙሪያ ገ ጠም ቀውስ ለመውጣት የሃገራችን ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ዜጎች ሁሉ የአለንበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ስሌት ውስጥ በማስገባት ራስን ሆነ ድርጅትን ሳይሆን ህዝብንና ሃገርን በሚያስቀድም መንፈስ መወያየት ይኖርባቸዋል ከሚል ፅኑ እምነት በመነሳት እንዲህ አይነ ቱን ውይይት ለማገዝ በዚህ ጉዳይ ያለውን ሃሳብ ያቀርባል።

በመሰረቱ ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ የተያዘው ትግል ህዝባችንን ማእከል አድርጎ ካልተካሄደ የትም የሚያደርስ አይሆንም የ ሚለው አስተሳሰብ ቢያንስ በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ ሁሉም የሚያምንበት እንደሆነ ግልፅ ይመስለናል። ከዚህም እምነት በመነሳት ምን ም እንኳን ሁልጊዜም ከህብረተሰባችን ተጨባጭና አወንታዊ መልስ ባያገኙም የተነስ ታገል ጥሪዎች ለህዝቡ በተደጋጋሚ ሲስተጋ ቡ ቆይተዋል። አንዳንዴ እንደ ግንቦት ጥሪውን ሰምቶ ህዝባችን በሚልዮን እየተቆጠረ ተንቀሳቅሶ በፀረ ህዝብ አመፅና ሽብር ከዚ ያም ባላነሰ ሁኔታ በአመራር ክፍተት ንቅናቄው መልሶ የሚከስምበት ሁኔታ ሲከሰት ታዝበናል። እንዲህ አይነቱ መክሸፍ ሲከሰት ደግሞ በድህረ ግንቦቱ ሂደት በግልፅ እንዳየነው በህብረተሰቡ ድቅድቅ ያለ የጨለምተኝነትና የትጥቅ መፍታት አባዜ ይከተላል። ይህንን ችግር ከስሌት ሳያስገቡ የሚሰነዛሩ የተነስ ታገል ጥሪዎች ደግሞ ከህዝባችን የአወንታዊ መልስ የፍንጭ ፍንጭ ሳያገኙ እ የቀሩ ይህንኑ የትጥቅ መፍታት አባዜ እያገዙ ህብረተሰቡ የማይወጣው የጨለምተኝነት አዙሪት ውስጥ የሚዘፈቅበት ሁኔታ ታዝበ ናል።

ከዚህ ስንነሳ መጀመሪያ እናምንበታለን የምንለውን የህዝባዊ ትግል እምርታ ለመቀስቀስ ምን እናድርግ? ከዚያ ደግሞ ይህ የተቀሰቀሰ የህዝባዊ ትግል እምርታ እንዳለፈው በሽብርና በአመራር ክፍተት መልሶ እንዳይከስም ከወዲሁ እንዴት እንዘጋጅ? የ ሚሉትን ሁለት ጥያቄዎች በሚገባ መመለስ ለቀጣዩ ትግላችን ወሳኝ ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚህ ደግሞ ከአለፈው ትግላችን ትምህር ት ቀስመን እንራመድ ካልን የመጀመሪያ መጀመሪያ ተግባራችን ዛሬ በሃገራችን በህዝባዊና ፀረ ህዝብ ሰፈሮች መሃከል ያለው የሃ ይል ሚዛን በሃገር ውስጥም ሆነ በአካባቢና በአለም አቀፍ ደረጃ ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ አንስተን መመለስ ይኖርብናል።

በሃገር ደረጃ እኔ ከስልጣን ከወረድሁ ኢትዮጵያ እንደ ሃገር የመቀጠሏ ነገር የማይታሰብ ይሆናል እያለ ነጋ ጠባ የሚዝ ት ገንጣይ አስገንጣይ ቡድን በመንግስትነት ተኮፍሶ ለአንድነት የቆሙ ሃይሎች ደግሞ ከነድክመታቸውና ክፍፍላቸው በተቃዋሚነ ት የተሰለፉበት በታሪካችን ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነን። እርግጥ ይህ ሃይል የወያኔ/ኢህአዴግ መ ሪዎች እንደሚሉት ከዳር እስከዳር በህዝብ የተደገፈ አይደለም። ግን ግሞ በተቃዋሚው ጎራ እንደሚባለው በህዝቡ ከዳር ዳር የ

ተተፋና ለመውደቅ አንድ ሃሙስ የቀረው ሃይል ነው ማለት አይቻልም። በተለይ ከግንቦት 97 ውድቀቱ አስፈላጊውን ትምህርት ቀስሞ ከዋና ደጋፊዎቹ/ተጠቃሚዎቹ በተጨማሪ ትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች በማቅረብ ከህብረተ ሰቡ የተወሰነ ሃይል (በተለይ በወጣቱ አካባቢ) እየመለመለና እያደራጀ በመሄድ ላይ ይገኛል። በዚህ ላይ ደግሞ በመሬት ስሪቱ ሳቢያ የሃገሪቱን ገበሬዎች "በደጋፊነት" እጅ ተወርች አስሮ የያዘ፣ ከአዲስ አበባ እስከ ዳር ድንበር መንደር ድረስ ድርጅታዊ መዋቅሩን የዘረጋ፣ ሰራዊቱን፣ ደህንነቱን፣ የመንግስቱን በጀት ከቁጥጥሩ ስር በማድረግ ህልውናውን ለማረጋገጥ ከምንም የማይመለስ ሃይል ነው።

በአለም አቀፍና በአካባቢ ደረጃም ያለው ሁኔታ በነባር ችግሮች ላይ ትግላችንን ይበልጥ አስቸጋሪና ውስብስብ የሚያደርጉ አዳዲስ ክስተቶች አሉ። ነባር ችግሮች ሊባሉ ከሚችሉት ውስጥ በአካባቢያችን ደረጃ አንዲት ዴሞክራሲያዊትና ጠንካራ ኢትዮጵያ ለሚለው አጀንዳ ሊቆም የሚችል ማንም ሌላ ሃገር ወይም ሃይል አለመኖሩ አለ። እነዚህ የአካባቢ ሃይሎች ትላንት ወያኔና ሸአብያ ሃገራችንን ለመከፋፈልና ለማዳከም ሲሰሩ ሙሉ ድጋፍ ይሰጡዋቸው እንደነበረ የታሪክ ሃቅ ነው። ዛሬ የኛ የተቃዋሚዎች አጀንዳ የነሱን ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ተፃርሮ የቆመ በመሆኑ ከነዚህ አካባቢ ሃይሎች ድጋፍ ሳይጠይቅም ሳያገኝም ብቻ ሳይሆን የነሱንም ስውር ደባ እየተቋቋመ የሚካሄድ ትግል ነው።

በአጠቃላይ የአለም አቀፍ ሁኔታም አንፃር ሲታይ ደግሞ በተለይ ከግሎባላይዜሽን ጋር ተያይዞ የተከሰተው ሁኔታ አዳዲስ ጠላቶች ፈልፍሎብናል። እንደሚታወቀው በንጉሱም ሆነ በርግ ዘመን በሃገራችን የውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት የስትራቴጂ እንጂ እስከዚህም የኢኮኖሚ ብዝበዛ ገፅታ አልነበረውም። የአሜሪካም ሆነ የሶቭየት ተስፋፊዎች ዋና አላማ በነበረው የቀዝቃዛ ጦርነት ሁኔታ በዚች በቀይ ባህር አካባቢ ቁልፍ ቦታ በያዘች አገር የመተከል አላማ ነበር። ዛሬ ይህ ሁኔታ ጨርሶ ተቀይሯል። በተለይ በመሬት መቀራመቱ ሳቢያ እንደምናየው ከሆነ "አዲሶቹ ቅኝ ገዥዎች" ወደ ሃገራችን የሚጎርፉት ለኢኮኖሚ ብዝበዛ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ለብሄራዊ ነፃነቱና ብዝበዛን ተቃውሞ በብሄራዊ ልማት ላይ ያተኮረ አካሄድ ብሎ ነገ በጥቅም በተንበረከኩላቸው ባንዳ ልሁቃን ላይ ትግሉን ቢያፋፍም ይህ ፍልሚያ ከነዚህ ወገኖች ጋር ብቻ አይሆንም። አዲሶቹ ቅኝ ገዥዎች ወገን ለይተው በፖለቲካ፣ በፋይናንስ፣ በሚሊታሪው መስክ በፀረ ህዝቦቹ ወገን ተሰልፈው ሃገራችንን የሚያደሙበት ሁኔታ ይኖራል።

ከዚህ የሃይሎች አሰላለፍ አንፃር የኛስ የዴሞክራቶችና የሃገር ወዳዶች ጎራ ድካምና ጥንካሬ ምን ይመስላል? እንደ ፀረ ህዝቦቹ የገንዘብና የማቴርያል አቅም የለውም። እንደ እነሱ በሚሊታሪው፣ በደህንነቱ፣ በድርጅቱ ሃገሪቱን የሚያላብስ ድርጅታዊ ሃይል የለውም። ሃገራዊና ዴሞክራሲያዊ አጀንዳ ስላለው እንደ እነሱ የሚተማመንበት ምንም አይነት የውጭ ሃይሎች ድጋፍ የለውም። ራሳችንን እናታልል ካላልን ደግሞ ዛሬ በአለው ተጨባጭ ሁኔታ በታሪካችን ከዚህ ቀደም ባልታየ መልክ በህዝባችን ፊት የተአማኒነት ችግር አለበት። ከነዚህ ሁሉ የድክመት መነሾዎች አንፃር ግን አንድ ወሳኝ የሆነ የጥንካሬ ምንጭ አለው። ይኸውም የተአማኒነቱን ችግር ከተወጣ በፀረ ህዝብ ፖለቲካቸው የተነሳ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች በምንም አይነት ሊደርሱበት የማይችሉትን ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ይዞ መንቀሳቀስ መቻሉ ነው።

የውስጡም ሆነ የአለም አቀፉና የአካባቢው ሁኔታ ለአንዲት ዴሞክራሲያዊትና ጠንካራ ኢትዮጵያ ለሚደረግ ትግል የተመቸ አይደለም ሲባል ግን ይህ አስቸጋሪነት ተስፋ የሚያስቆርጠን አይደለም። እንዲያውም ስለቀጣዩ የትግል አቅጣጫችንና ተግባሮቻችን ምንነት የጥራት ምንጭ ነው እንላለን። እነዚህን የጥፋት ሃይሎች ለመቋቋም ትግላችን በነሱና በጥቂት "ግንባር ቀደም" ሃይሎች ወይም ድርጅቶች መሃከል የሚደረግ ግርግር መሆን የለበትም። በተጨባጭ ካለው የሃይሎች አሰላለፍ ከተነሳን ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ የሃገራችን እጣ ፈንታ በሌላ በማንም ሳይሆን በህዝባችን ትከሻ ላይ የወደቀበት ሁኔታ ውስጥ እንዳለን መረዳት አስቸጋሪ አይደለም። በዚህም የተነሳ ከአለንበት ችግር ወጥተን ወደፊት ለመራመድ ሌላ ምንም መፍትሄ አይኖረንም። የአለን አንድ መፍትሄ ህዝባችን የትግሉ ባለቤትነት ተሰምቶት እንደ የካቲት አፍላ ወቅትና እንደ ግንቦት 97 በሚልዮን እየተቆጠረ እንደገና እንዲንቀሳቀስ ከዚያም ደግሞ ይህ ትግሉ አሁንም እንደ የካቲትና ግንቦት መልሶ ከስሞ ሃገራችን የባሰ የቀውሶች አዙሪት ወስጥ እንዳትገባ እንዴት እንራመድ? በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ በወጉ ተወያይተን የጋራ ትግል ስትራቴጂ መንደፍ ብቻ ነው።

ለዚህ ደግሞ የመጀመሪያ መጀመሪያ ሊባል የሚችለው ተግባራችን ስትራቴጂያዊ አላማችንን በግልፅ ማስቀመጥና ወደዚህ በሚደረገው የትግል ጉዞ የነገሮችን ቅደም ተከተል እንደዚሁ በግልፅ የሚያስቀምጥ ሮድ ማፕ ነድፈን ለታጋዩ ህዝብ ማስጨበጥ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ የወያኔ ኢህአዴግ ሸብርና አፈና ከታጋዩ ህዝብ አእምሮ ሊፍቀው በማይችለው ሁኔታ በህዝቡ አእምሮ መስረፅ የሚኖርበት አላማና ሮድ ማፕ ይዘቱ ምንድን ነው?

ስትራቴጂያዊ አላማችንን በተመለከተ እምብዛም ችግር ያለ አይመስለንም። ዛሬ ባለው ሁኔታ ዴሞክራት ነኝ፣ አገር ወዳድ ነኝ ብሎ እርቀ ሰላም የወረደባት አንዲት ዴሞክራሲያዊት፣ ጠንካራና ፊቷን ወደ ልማት ያዞረች እናት አገር መመስረት የሚለውን አላማ የማይደግፍና ለዚህ እታገላለሁ የማይል ማንም የለም። ከዚህ ይልቅ ሰፊና የሰከነ ውይይት ተካሂዶ በግልፅ መመለስ ያለበት ወደዚህ ክቡር አላማ በሚደረገው የትግል ጉዞ የነገሮች ቅደም ተከተል ወይም የምንከተለው ሮድ ማፕ ምን ይሁን የሚለው ጥያቄ ነው።

በኛ እምነት በአሁኑ ወቅት ሁሉም አንግቦ መንቀሳቀስ ያለበትና ትግላችንን ወሳኝ የሆነ ምእራፍ ሊያደርስ የሚችለው አጀንዳ የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ በህዝባዊ የትግል ማእበል ከተያያዘው የጥፋት ሂደት እንዲያፈገፍግ ተገዶ በሃገራችን "የዴሞክራሲያዊ ሽግግር አገር አቀፍ ጉባኤ" የሚሰየምበትን ሁኔታ የማመቻቸት አጀንዳ መሆን ይኖርበታል እንላለን። በዚህ በዴሞክራሲያዊ

ሽግግር አገር አቀፍ ጉባኤ ጉዳይ በተለይም ተሳታፊዎቹን፣ ሽግግሩን ለማሳካት የሚጠብቁትን አጣዳፊና ዘላቂ ተግባራት፣ ለነዚህ እውንነት የሚያቋቁማቸውን ልዩ ልዩ የሽግግር ኮሚሽኖች ወዘተ ከወዲሁ ግልፅ ስእል ይዘን መንቀሳቀስ ይኖርብናል። እነዚህ ነጥቦች በምርጫ 97 ወቅት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት (ኢዴሃህ) አማራጭ ሰነድ በሰፊው ተተንትነው ቀርበዋል። ዛሬም ቢሆን ከዚህ ሌላ አካሄድ ስለማይኖርና ወደፊትም በሰፊው ስለምንመለስበት እዚህ ላይ ለጊዜው ዝርዝር አንገባበትም። አንድ ከወዲሁ በግልፅ መቀመጥ ያለበት ጉዳይ ቢኖር እንደምንመኘው ከአለንበት አስቸጋሪ ቀውስ ወጥተን የህዝባዊ ትግል እምርታ መቀስቀስ ከቻልን ትግላችን ተቀነባብሮ እንዲቀጥልና ለድል እንዲበቃ ይህ ወሳኝ የሆነ አገር አቀፍ የሽግግር ጉባኤ አጀንዳ ከወዲሁ በህዝባችን አእምሮ ተሰርፆ የትግል መሳሪያ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል የሚለው ነጥብ ነው። በዚህ ጉዳይ ወደፊት በሰፊው ስለምንመለስበት አሁን ደግሞ ወደ ሌሎቹ ወሳኝ ጥያቄዎች እንዙር።

የስትራቴጂያዊ አላማና የሮድ ማፕ ጉዳይ ከተቀመጠ ወዲያውኑ የሚቀርበው ጥያቄ ለነዚህ እውንነት እንደ ህይዎት እስትንፋስ አስፈላጊ የሚሆነው የህዝባዊ ትግል ማእበል እምርታ እንዴት ይቀሰቀስ? የሚለው ጥያቄ የሆናል።

ህዝባዊ የትግል እምርታ ለመቀስቀስ ምን መፈክሮች አንግበን እንነሳ? በህብረተሰቡ ውስጥ አስከፊ ጨለምተኝነትና የተጥቅ መፍታት አባዜ በተከሰተበትና ህዝባችን ይህ ነው በማይባል የህልውና ቀውስ ውስጥ በወደቀበት ሁኔታ በደፈናው "ለዴሞክራሲ" ወይም "ወያኔን ለመጣል" ከሚሉ ለጊዜው "ከሰማይ የራቁ" ከሚመስሉ መፈክሮች ዘልቀን የህዝቡን የህልውና ጭንቀቶች በሚያነግቡ መፈክሮች ዙሪያ መንቀሳቀስ ይኖርብናል። ይህ ማለት ደግሞ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ብሶታቸውን እያነገቡ ወደ ትግሉ የሚገቡበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል ማለት ነው። ይህ እንዲሆን ደግሞ በህጋዊነትም ሆነ በህቡእ ከሚንቀሳቀሱ ሃይሎች በተጨማሪ የነዚህን ክፍሎች ብሶቶች የሚጋሩና ጥያቄዎቻቸውንና መፍትሄዎቹን ጠቁመው ለትግል የሚጠሩ "ውስጥ አዋቂ" ዜጎች ሲቻል በይፋ ሳይቻል ደግሞ በህቡእ እየተደራጁ ተንቀሳቅሰው የሚያንቀሳቅሱ ዜጎች ያስፈልጉናል ማለት ነው።

በዚህ መልክ ሁሉም በየፊናው ብሶቱን እያነገበ ወደ ትግሉ መደባለቁ ብቻውን በቂ አይሆንም። የህዝባዊ ትግል ማእበል እምርታ እንፍጠር ካልን ሌሎች ሁለት ቁምነገሮች ይኖራሉ። መጀመሪያ እነዚህ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ የተለያዩ የህብረተብ ክፍሎች ብሶትህ ብሶቴ በሚል መንፈስ ትግላቸውን የሚያስተባብሩበት ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርብናል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ለእነዚህ የተሰበጣጠሩ ችግሮች ዘላቂ የሆነ መፍትሄ ከተፈለገ የስርአት ለውጥ የግድ አስፈላጊ መሆኑን በአላሰለሰ ቅስቀሳ ታጋዩ ህዝብ እንዲገነዘብ በማድረግ የትግሉ የፖለቲካ ገፅታ ከእለት እለት እየጎላ የሚሄድበት ሁኔታ መፍጠር ያስፈልገናል።

የትግል አጀንዳችንና አካሄዳችንን በተመለከተ በዚህ መልክ የምናደርገው የእይታ ለውጥ የምንመኘውን በጎ እምርታ እንዲፈጥር ከፈለግን የአደረጃጀት ለውጥም ያስፈልገናል። በተለይም በሃገሪቱ ውስጥ በይፋ የሚታገሉ ሃይሎች "መደበኛ" ሊባል ከሚችለው ፖለቲካ ተኮር አደረጃጀት ዘልቀው መሄድ ይጠበቅባቸዋል። እስካሁን እንደታየው ከሆነ አንድ ድርጅት ሲቋቋም ፕሬዜዳንት፣ ምክትል ፕሬዜዳንት፣ ዋና ፀሃፊ፣ ገንዘብ ያዥ፣ የውጭ ግንኙነት፣ የህዝብ ግንኙነት ወዘተ ከሚለው የዘለቀ "ዘርፈ ብዙ" አደረጃጃጀት የላቸውም። የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ብሶታቸውንና አማራጮቻቸውን አንግበው ወደ ትግሉ ይደባለቁ ካልን ለትግሉ አመራር እንሰጣለን ብለው የሚነሱ ሃይሎች እነዚህን እጅግ የተሰበጣጠሩ ችግሮች ከወያኔ/ኢህአዴግ ፀረ ህዝብ ፖሊሲዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት አጉልቶ እያሳየ ብቻ ሳይሆን ያሉትን ህዝባዊ አማራጮች እየጠቆመ ያላሰለሰ እንቅስቃሴ የሚያደርግ "ባለቤት" የሚመድብ የአደረጃጀት ስልት ያስፈልጋቸዋል። በዳበሩት ዴሞክራሲዎች እንደምናየው ከሆነ ፓርቲዎች ሲደራጁ በስልጣን ላይ ያለውን ድርጅትና ፖሊሲዎቹን እያወገዙ ተከታታይነትና ተአማኒነት በአለው መልክ ለህዝቡ አማራጭ ለማቅረብ በመንግስቱ ሚኒስቴሮችና ተቋማት በተጓዳኝ የሚሰሩ የተሰበጣጠሩ ኮሚቴዎች አላቸው። በእንግሊዝ አገር ብንሄድ ተቃዋሚው ፓርቲ "ሻዶ ካቢኔት" በሚል መልክ ራሱን እንደ መንግስት አዋቅሮ ይንቀሳቀሳል። በሌሎቹም ዴሞክራሲያዊ አገሮች ብንሄድ እንደ እንግሊዝ አገር "ተተኪ መንግስት" ባይሉትም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በየዘርፉ ለህዝቡ ተጨባጭ አማራጮች እያቀረቡ ትግላቸውን ለማካሄድ እንደዚሁ ዘርፈ ብዙ የሆነ የአደረጃጀት ዘይቤ ይከተላሉ።

በኛም አገር ከደፈና ፖለቲካዊ መፈክሮች ዘልቀን የህዝብን አመኔታ የሚያገኝ ስራ እንስራ ካልን እንዲህ አይነቱ ዘርፈ ብዙ አደረጃጀት ያስፈልገናል። የመሬት ስሪቱን ለመዋጋት ከወያኔ/ኢህአዴግ የገጠር ልማት ሚኒስቴር አኳያ በተቃዋሚውም ድርጅት ውስጥ የዚህ ዘርፍ ተጠሪ ያስፈልገዋል። በዚህ መልክ እየከፋና እየሰፋ በመሄድ ላይ ያለውን ድህነት፣ በተለይም የወጣቱን የጅምላ ስራ አጥነት፣ የኑሮ ውድነትን፣ የአካባቢ ውድመትን፣ ነጋዴውንና ኢንቬስተሩን እጅ ተወርች ያሰሩትን አድላዊና ሙሰኛ ፖሊሲዎች ወዘተ እየተከታተሉ በበጎ አማራጮች ዙሪያ እነዚህን ክፍሎች ወደ ትግሉ ለመሳብ የሚሰሩ አካላት መመደቡ ለቅስቀሳችን ተጨባጭነትና ተአማኒነት የሚሰጥ አካሄድ ይሆናል ማለት ነው።

እርግጥ ለእንዲህ አይነቱ አደረጃጀት እውንነት ጉልበቱስ፣ አቅሙስ ከየት ይመጣል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በእኛ እምነት ይህ እስከዚህም አስቸጋሪ አይመስለንም። እንዲያውም ጉልበትና አቅም እያባከነ ያለው የእስካሁኑ አደረጃጀት ነው ለማለት ይቻላል። ግንቦት ሰባት፣ ሸንጎ፣ የሽግግር ጉባኤ፣ ጥምረት ወዘተ እያልን ስብሰቦች ስናበራክት አምስት ፕሬዜዳንቶች፣ አምስት ፀሃፊዎች፣ አምስት ገንዘብ ያዦች፣ ያንኑ አንድ ፀረ ኢህአዴግ መልእክት ለማስተላለፍ አምስት የውጭ ግንኙነት ተጠሪዎች የሚለው አካሄድ ጊዜና ጉልበት በወጉ የሚጠቀም አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ እንዲህ አይነቱን አደረጃርጀት እውን ለማድረግ ብዙ ጊዜ ይወስዳል የሚል ስጋት ሊኖር ይችላል። አወን ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ግን ደግሞ ለአለፉት ሃያ አመታት የፀረ ኢህአ

ዴግ ትግላችንን ዘወር ብለን ስንቃኝ አካሄዳችን ጊዜ መውሰድ ብቻ ሳይሆን ጊዜ የማባከን አካሄድ እንደሆነ እናያለን። የሚያስፈልገንን የህዝባዊ ትግል እምርታ ለመቀስቀስ ወዴትና እንዴት እንደምንሄድ ግልፅ ስእል ኖሮን እስከተንቀሳቀስን ድረስ ከጊዜ ጋር ከእለት እለት ወደ ግባችን ለመድረስ ሁኔታዎችን እያመቻቸን ስለሆነ ይህ ትልቅ ችግር ሆኖ መቅረብ ያለበት አይመስለንም።

ይህ ሁሉ ከተባለ ዘንዳ ለአላማችን ግብ መምታት በዚህ መልክ የተቀሰቀሰው የህዝባዊ ትግል እምርታ ተመልሶ ከመክሰም ይልቅ ቀጣይነት ኖሮት ለድል እንዲበቃ ምን አይነት አካሄድ ያስፈልገናል የሚለው ጥያቄ ይነሳል። በዚህ ወሳኝ ጥያቄ ያለንን አስተሳሰብ በቀጣይ ፅሁፍ ለውይይት እናቀርባለን።

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)
ጥቅምት 2006 ዓ.ም.